# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 39 የካቲት 5 2001 ዓ.ም


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

## አሜሪካዊው ዲፕሎማት በመኖርያ ቤቱ ሞቶ ተገኘ

ባሳለፍነው ቅዳሜ በአዲስ አበባ በአሜሪካ ኤንባሲ የውጭ ጉዳይ ኦፊሰር የነበረው ሚስተር አድኪንስ በመኖሪያ ቤቱ ሞቶመገኘቱ ሮይተርስ የተባለው የዜና አውታር የገለጸ ሲሆን ያሟሟቱ ሁኔታ ግልጽ እንዳልሆነና በጥናት ላይ መሆኑ የኤንባሲው ባለስልጣናት መግለጻቸውን አስታውቋል።

የዜና አውታሩ በማስቀጠልም የአሜሪካ መንግስት ጉዳዩን ከወያኔ ባለስልጣናት ጋር በመተባበር በማጥናት ላይ መሆናቸውን አንድ ጉዳይ ዩፋ እስኪሆን ድረስ ስሙ እንዳይገለጽ የፈለገ ዲፕሎማት ገልጿል። ሌላው የአሜሪካ ዲፕሎማት ደግሞ ሆን ተብሎ የተፈጸመ ግድያ ነው ብለው እንደሚጠረጥሩና የአሜሪካ የደህንነት አባላት ጉዳዩን በማጥናት ላይ እንደሚገኙ አስታውቋል።

ዘጋቢያችን ያናገራቸው አንድ ዲፕሎማት ነገሩ በዚህ የአሜሪካ ከፍተኛ ባለስልጣን በኢትዮጵያ ያለውን ችግር ለማጥናት በመጣበትና ተቃዋሚዎችን ባናገረበት ሰአት መሁኑ ተራ ገጠመኝ ሳይሆን ሆን ተብሎ አገዛዙ ላይ ባሉ ሰዎች የተቀነባበረ ነው ብለው ብዙዎቹ የኤንባሲው ዲፕሎማቶች እንደሚያምኑ ገልጸው ለማንኛውም ምርመራ እየተካሄደ ስለሆነ የመጨረሻውን ውጤት ማየት እንደቸኮሉ ገልጸዋል።

### ማስታወቂያ

ዛሬ በግንቦት7 ንቅናቄ ውስጥ የተሰባሰብነው ግለሰቦች ሃገራችን ወደሌላ የአመጽ አዙሪት እንዳትገባ ከምር ተጨንቀን፣ አንቸኩል! ለወያኔ እድል እንስጠው፤ ግድ የላችሁም እነዚህ ሰዎች የእዚችው ሃገር ዜጎች ናቸው ውለው አድረው ለሀገራችን በጎ መመኘታቸው አይቀረም ብለን ብዙዎች እስከሚታዘቡን መሟገታችንን ----ያውቃሉ?

ሸህ ግዜ ቀናውን፣ ሸህ ግዜ የሰላሙን መንገድ ብንመኘው፣ ሸህ ግዜ እረ ተው፣ ይህች ሃገርና ሁላችንም በጥፋት አዙሪት ውስጥ መድፈቁ ይብቃን ብለን ብንማጸን፤ ከእዚህም አልፎ ተርፎ በታሪካችን አድርገን የማናውቀውን፣ ለሰላም ካለን ጽኑ ፍላጎት ተነስተን፣ በሃገራችን ላይ የተሰራውን በደል ወደ ጎን አድርገን፣ በነጻነታችን ተደራድረን ለእረቅ ለስምምነት ጉሮሯችን እስኪደርቅ በመወትወታችን ፣ ከመለስ ዜናዊና ከጓደኞቹ ያገኘነው ምላሽ፣ እየገዘፈ የሚሄድ ዘረኛነት እብሪትና ንቀት እንደሆነ እርስዎስ ቢሆን ሳይታዘቡት አይቀርም፡፡

እነዚህ ዘረኛ እብሪተኞች ትእግስታችንና ተማጽኗችንን ከፍርሀት የሚቆጥር፣ ያለእኛ ደፋር የለም እንዲሉ አድርጎ የሚያይ በባሩድ ሽታ የሰከረ ህሊና ያላቸው መሆናቸውን እርስዎም እንደኛ ሳይረዱት አይቀርም፡፡

በተደጋጋሚ ኢትዮጵያዊ ስሜት ያላቸውን ዜጎች ማሰቃየት ማዋረድና ማዋከብ ስራ ብለው ተያይዘውታል፡፡ የቅረቡ ሰለባቸው ቴዲ አፍሮ የሆነበት ምክንያት የሚነሳው ከእዚሁ ለኢትዮጵያ ካላቸው ጥላቻ ነው፡፡ በልምና በምልጃ ስለሰላምና እርቅ በመስበክ የለየላቸው አረመኔዎችን ወደ ቀና ጎዳና መመለስ ይቻላል ብለን እኛ በግነብት ሰባት ውስጥ የተሰባሰብን ወገኖዎችዎ አናምንም፡፡ ይህንን እምነታችንን የሚጋሩ ከሆነ! ይነሱ ይቁሙ እኔንም በቃኝ ውርደት ብለው ከቆሙቱ ጎን ቁጠሩኝ ይበሉ፡፡

የግንቦት7 ንቅናቄን ሁለ ገብ ትግል ይደግፉ፡፡ ለእዚህ ትግል ማራመጇ ግንቦት ሰባት ይሆን ዘንድ ግንቦት 7 የጀመረውን የገንዝብ ማሰባሰብ ስራ ያግዙ፡፡ ሌላውም እንዲተባበር ያስተባብሩ፡፡

ግንቦት 7 ለፍህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ

## መጸህፉ ወያኔዎችን በንዴት አብግኗል፤በደራሲው ላይም የዛቻ መልእክት ተላለፈ

በጸረ-ኢትዮጵያዊነቱ በሚታወቀው በወያኔ ጋሻ ጃግሬ በበረከት ስምኦን እንደሚታዘዙ በሚነገርላቸው በአቶ ሴኩ ቱሬ በኩል አቶ ተስፋዬ ገብረአብ ድርጅቱን እንደካዱና በዚህም ሁሉም የድርጅቱ አባላት እንደተበሳጩ የሚገልጽ ምልእክት በድህረገጻቸው ማውጣታቸው ተገለጸ።

አቶ ተስፋዬ ገብረአብ ቀሪ ህይወታቸውን በሰሩት ስራ ሲጸጸቱ እንደሚኖሩ የገለጸው ይሄው በአቶ ሴኩ ቱሬ በኩል የወጣው መልእክት በማስቀጠልም ድርጊቱ ድርጅቱንና በድርጅቱ ለዘመናት ሲታገሉ የቀዩትን አባሎችን ሁሉ የሚያሳዝን የክህደት ወንጀል ነው በማለት ገልጾታል። በስተመጨረሻም በምንም ተአምር አታመልጠንም በሚል ከባድ የዛቻ ቃል መልእክታቸውን አጠናቀዋል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በትግራይ የዲሞክራሲ ጭላንጭል ታየ ፤ ቁጥሩ በርካታ ህዝብ የአረና ፓርቲ በጠራው ስብሰባ ላይ ተገኘ

አረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ለሉዓላዊነት በሚል ስያሜ የተቋቋመውና በሕወሃት ከፍተኛ አመራር በነበሩ ሰዎችን የተቋቋመው ድርጅት ጥር 24 ቀን 2001 ዓ.ም በመቀሌ የጠራው ታላቅ ህዝባዊ ስብሰብ በተሳካ መልኩ ማካሄዱ የአሜሪካ ድምጽ ዘግቧል።በስብሰባው ላይ ከዚ ቀደም ወያኔ በሚጠራው ስብሰባ ላይ ከሚገኘው የህዝብ ቁጠር እጅግ በርካታ ህዝብ የወያኔን አፈና ሳይፈራ የተአተፈበት ሲሆን የድርጅቱ ሊቀመንበር አቶ ገብሩ አስራት የድርጅቱን አላማና አደረጃጀት ያስረዱ መሆኑን አያይዞ ዘግቧል።

በስብሰባው ላይ ወያኔ የላካቸው አፍራሽ ሀይሎች ስብሰባውን ለመበተን ሙከራ ያደረጉ ሲሆን በስብሰባው ተሳታፊዎች መክሸፉም ተገልጿል;፡ ይህ ወያኔ ስልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ታይቶ የማይታወቅ ስብሰባ የትግራይ ተውላጆች ወያኔ ከጨነባቸው ፍርሀትና አፈና የተላቀቁና እንደሌሎች ወንድሞቻቸው የወያኔን አፍራሽ ደባ ለማክሸፍ በጋራ እንዲንቀሳቀሱ የሚያደርግ ቀስቃሽ መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔ፤ ሼህ ኤልያስና የእስልምናው ምክርቤት

የአዲስ አበባ እስልምና ምክርቤት በምርጫ 97 በተፈጠረው ግርግር ምክንያት ስልጣናቸው ተራዝሞ የቆዩትና ከወያኔ ጋር ባላቸው ትሥር በእስልምና እምነት ተከታዮች ተቀባይነት በሌላቸው በሼክ ኤልያስ ሬድዋን የሚመራውን ኮሚቴ ምክርቤቱ ሰሞኑን ባካሄደው ስብሰባ ሙሉ በሙሉ መበተኑ ተዘገበ።

ቀደምሲል አደርጅ ኮሚቴ ተቋቋሙ ከወረዳ የምክር ቤቱ አባላት ጋር ውይይት በማድረግ አመራሮቹ በዘመናቸው ባሳዩት የአመራር ድክመት ሙሉ በሙሉ መወገድ አለባቸው የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ ሲሆን በምትኩ አዲስ አባላት መመረጥ የሚል ሃሳብ ለጠቅላላው ኮሚቴ ማቅረባቸው ታውቋል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

# ርእሰ አንቀጽ

## ትብብር፣ የዴሞክራሲና የነጻነት እጣችን ውሉን እንዳይስት መቋጠሪያችን ነው፡፡

ወያኔ በጨነቀው ቁጥር የህዝቡ ትኩረት ወደ ህይወቱና አገዛዙ እንዳይሆን የሚሸርባቸው ተንኮሎች ማለቂያ የላቸውም ። በግንቦት ሰባት ምርጫ ሽንፈት ማግስት፣ የአክራሪ ሙስሊሞችን አደጋ ለመከላከል በሚል ሽፋን፣ ዘው ብሎ ሰራዊቱን ባይዶዋ ሱማሌ አስገባ ። እዚያው በዚያው ደግሞ፣ በጅማ፣ በከፋ፣ በወለጋ በክርስትያንና በሙስሊሞች ኢትዮጵያውያን ዜጎች መሃል ጠላትነት ያለ ለማስመሰል፣ በራሱ ካድሬዎችና ታጣቂዎች አዝማችነት ግድያዎችን ፈፀመ ። በሱማሌ ሽንፈት ሲገጥመውና ተዋርዶ መባረር የማይቀር መሆኑን ሲያይ፣ ከራሱ ፓርላማና የጦር ሃይል ጀርባ በምስጢር፣ የምዕራብ ኢትዮጵያን ድንበር ለርካሽ ዘይትና ለፖለቲካ ድጋፍ ሲል ለሱዳን ቸበቸበ ። በስልጣን ላይ ተፈናጦ የነቀዝ ሆዱን ከመሙላት በቀር፣ ሃገራዊ ርዕይም ሆነ ህዝባዊ አላማ የሌለው ይህ አውዳሚ ሃይል፣ በህዝቦች የተባበረ ትግል ካልተንበረከከ በቀር፣ የሚቀፈቅፋቸው ተንኮሎች ማክተሚያ የላቸውም እንላለን ። በዚህ አይነት አደገኛ ጠላት ፊት፣ እርሱ በየጊዜው በሚረውራቸው ቅልጥሞች እርስ በርስ መሻኮት ሳይሆን፣ ሊያስማሙ በሚችሉ ዝቅተኛ መሰረቶች ላይ ቆሞ፣ የአምባገነንነትን ፍፃሜ ማቃረብ ነው ። ኢትዮጵያን ይህን ከመሰለ ተውሳክ ለማፅዳት፣ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ የማይፈነቅለው ደንጊያ፣ የማይበጥሰው ቅጠል አይኖርም ። ለትብብር ጥሪውን የማያቀርብለት ሃይል አይኖርም፡፡

ይህ የመተባበር አስፈለጊነት ሁሌምና ሁሉም የሚወተውተው ቢሆንም እንደ ዘንድሮ ግን የመተባበር አስፈላጊነትና የመተባበሪያ አጀንዳዎች ምንነት ለሁሉም ፍንትው ብሎ የታየበት ወቅት ያለ አይመስለንም፡፡ የቀረ ነገር ቢኖር ሁላችንም የምንለው አንድ አይነት ነገር መሆኑን ህዝብ እንዲያውቀውና በቃል ኪዳናችን እንዲያስረን ትብብር ለምን፣ በምን፣ ወዴትና እንዴት የሚሉትን ጥያቄዎች ለህዝብ በሚገባ ቋንቋ በማያሻሙ ቃላቶች ማስቀመጥ ነው፡፡

የግንቦት 7 ንቅናቄ የሃገራችን ህዝብ ምን እንደሚፈለግ በምርጫ 97 አረጋግጧል ብሎ ያምናል፡፡ ህዝብ የሚፈልገው እርሱ በፈቃዱ ውክልና ሰጥቶ ስልጣን የሚሰጠው መንግሰት ማቆም ብቻ ነው፡፡ ህዝብ ከ97ቱ ምርጫ ጋር ተያይዞ የከፈለውን መስዋእትነት ከፍሎም የሚመኘውን በምርጫው ያቆመውን መንግስት ለማየት ለምን እንዳልቻለ አጥርቶ ያውቃል ብለን እናምናለን፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም በሙሉ፣ በየትኛውም የህጋዊነትና ህገወጥነት ማእቀፍ ይካተቱ፣ የትኛውንም የትግልና የአደረጃጀት ስልት ይጠቀሙ ከእዚህ በኋላ ትግላቸው ህዝብ በ1997 ምርጫ የገለጸውን ፍላጎት ማስፈጸሚያ ከመሆን የላቀ ህዝባዊና ታሪካዊ አደራ ሊኖራቸው አይችልም ብሎ ግንቦት7 ያምናል፡፡

የግንቦት 7 ንቅናቄ የሃገራችን የፖለቲካ ሃይሎችና አጠቃላይ ህብረተሰቡ ሊያስማማ የሚችል የመጨረሻው የትብብር መሰረቶች ህዘብን የስልጣን ባለቤት እንዲሆን የሚያስችሉ ሁኔታዎችንን ማመቻቸት ነው ብሎ ደግሞ ደጋግሞ ወትውቷል፡፡ ትብብሮች፣ ህብረቶች፣ መድረኮች፣ ግንባሮችና ሌላም ስም ይሰጣቸው ሁሉም ይህን የተቀደሰ አላማ ይዘው እስከተነሱ ድረስ ግንቦት ሰባት እደጉ ተመንደጉ ጉዟችሁ የተቃና ይሁን ብሎ ይመርቃቸዋል፡፡ በየወቅቱም ህጋዊ በሆነው የፖለቲካ ምህዳር የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች በአንድነት ለመስራት ሲነሱ ግንቦት 7ን ደስ የሚለው ትብብሩ አቅም እንደሚሰጣቸው፣ ብሎም መሰረታዊ የሆነውን የህዝብ ጥያቄ በጋራ አንስተው ለመቆም ድፍረቱን ያጎናጽፋቸዋል በሎ ስለሚያምን ነው፡፡ በቅርቡ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ፣ መድረክ የተባለው ስብስብ አባል መሆኑን ሲገልጽ አበጀህ የምንለውም ለእዚህ ነው፡፡ ሌሎችም ህዝብን የስልጣን ባለቤት ለማድረግ ቆርጠው የተነሱ ተቃዋሚ ድርጅቶች የአንድነት ፈለግ ተከትለው የመድርኩ አባል በመሆን ወያኔ ሊከፋፍለው የማይችል ጠንካራ የተቃዋሚዎች ህብረት ቢፈጥሩ የሃገርና የህዝብን ሲቃይ ለማሳጠር ወሳኝ ይሆናል እንላላን፡፡

በግንቦት 7 በኩል ህጋዊ በሆነው ምህዳር የተሰባሰቡትን የተቃዋሚ ድርጅቶች ህብረት መቀላለቅል ባይችልም፤ ከሚመስሉ ወያኔ ህገ ወጥ ብሎ ከሚጠራቸው ድርጅቶች ጋር የሚያደርገው ህብረት ህዝብን የስልጣን ባለቤት ለማድረግ እንደሚሆን ደግሞ ደጋግሞ ገልጽዋል፡፡ ይህ እስከሆነ ድረስ፣ ምንም እንኳን የሃገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ አልፈቅድ ብሎ የተለያየን የፖለቲካ ስብስቦች በተለያዩ የአደረጃጀት ጅረቶች ብንፈስም መጨረሻችን ሁላችንም በሚያቅፈው የዴሞክራሲ ባህር ውስጥ ይሆናል የሚል የጸና እምነት አለን፡፡

ወያኔ ይህን የሁላችንንም ቁርጠኝነት ተረድቶ፣ ከእብሪቱ ቢታቀብና፣ ያሰራቸውን የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ ቢፈታ፣ በግፍ አስሮ የሚያሰቃያቸውን ብርቱካን ሚደቅሳንና ቴዲ አፍሮን እና ሌሎች የፖለቲካ እስረኞችን ሁሉ ሳይውል ሳያድር ቢለቅ፣ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ለሚያቀርቡለት የሙብት ጥያቄ ተገቢ ምልሽ በግዜ ቢሰጥ ለራሱ ይበጀዋል ባይ ነን፡፡ በአሻፈረኝ ባይነቱና ወሮበላነቱ ለመቀጠል ከወሰነ ግን፣ ወያኔን ከምድረ ገፅ ለማጥፋት ከሰይጣን ጋር መወዳጀት ካለብንም እናደርገዋለን ። ውርደትን ተቀብለን አሜን ብለን አንኖርም ። በሃገራችን ላይ በባርነት አንገብርም፣ የወያኔን ቅርሻት እያሸተትን አንገታችንን ደፍተን ልንኖር አይቻለንም ።

## ውድ አንባቢዎቻችን

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።**

g7radio@ginbot7.org

## መጸህፉ ወያኔዎችን...(ከገጽ 1 የዞረ)

የውስጥ ምንጮቻችን እንዳመለከቱን መጸህፉ ከወጣ ጀምሮ በወያኔዎች ካምፕ ውስጥ ከባድ መደናገጥና እርስ በርስ መጠራጠር እንደተፈጠረ ገልጸዋል። በማስቀጠልም መጸህፉ በተወሰኑ በድርጅቶ የበላይ አካላት ብቻ በድብቅ ሲሸረብና በብዙዎች የድርጅቱ አባላትና የንጹህ ኢትዮጽያውያንን ህይወትና ህልውና ለማጥፋት ሲፈጸም የነበረውን ደባ ለድርጅቱም አባላት እንዲሁም ለመላው የኢትዮጽያ ህዝብ በማሳወቅና የወያኔን ትክክለኛ ባህሪ በማሳየት ድርጅቱን ራቁቱን ማስቀረቱን ገልጸዋል።

"ይህ እያደር እየወጣ ያለው የድርጅቱ ሚስጥር ድርጅቱ የገባበትን የመናድ አደጋ ክብደት አጉልቶ የሚያሳይ ነው" ያሉት አንድ ዘጋቢያችን ያናገራቸው የፖለቲካ ተንታኝ "ብዙ የድርጅቱ ባለስልጣናትም ሁኔታዎች ሲመቻችላቸው ድርጅቱብን አጋልጠው ለመውጣት ዝግጁ እንደሁኖ ከሚያሳዩ በርካታ ምልክቶች አንዱ ከተወሰኑ ጊዜ ጀምሩ በድርጅቱ ስብሰባዎች ላይ በተጠናከረ መልኩ የሚታዩ የሃሳብ ልዩነቶች መስፋፋት ነው። ድርጅቱ ብዙም እድሜ የለውም" ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ውድ አንባቢዎቻችን የወያኔ ከፈተኛ ባለስልጣን የነበሩት አቶ ተስፋዬ ገብረአብ ባለፈው ወር የጋዜጠኛው ማስታወሻ በሚል የወያኔዎችን ድብቅና በተወሰኑ ሰዎች መሃከል ተይዘው የቆዩትን ሚስጥራት ሁሉ ያጋለጠ መጽሃፍ ማውጣታቸውና ለገበያ ማዋላቸውን ማሳወቃችን የታወሳል።

## ወያኔ፤ሼህ ...(ከገጽ 1 የዞረ)

በዚሁ መሠረት ኮሚቴው 11 አባላትን ያካተተ አመራር የሾመ ሲሆን ከነዚሁ መሃከል ሀጂ ኡመር እንድሪስና ሼህ ኑረዲን ይላል አዲስ አበባን በመወከል ለኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች አመራርነት መወከላቸው ታውቋል።

ይህን በማስመልከት የተጠየቁት ሼክ ሬድዋን የኮሚቴው ውሳኔ በደንቡ መሰረት ገና በወረቀት ስላልደረሰኝ አሁን መልሰ መስጠት እችገራለሁ። ነገሮች እንደሚባሉት ሄደው ከሆነ ግን አስፈላጊውን አስተዳደራዊ እርምጃ ለመውሰድ እንገደዳለን በማለት ዝርዝር መልሰ ከመስጠት የተቆጠቡ ቢሆንም ዘጋቢያችን ያናገራቸው የውስጥ አዋቂዎች ግን በጉዳዩ ላይ እጅግ መበሳጨታቸውንና ከወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር በጉዳዩ ላይ እየተመካከሩበት መሁኑን ለማወቅ ተችሏል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

## ሃይለ ሀሳብ

# የኢህአዴግ የእድገት ጭምብል በውጭ ምንዛሪ ቀውስ ሲጋለጥ

የዛሬ 18 ዓመት ገደማ የኢትዮጵያ ህዝብ በኢህአዴግ ጥረት በአሥር ዓመታት ውስጥ በቀን ሦስት ጊዜ መብላት እንደሚችል ተደስኩሮ ነበር:: ያ ህልም ቅዠት ከሆነ እነሆ ሌላ አሥር ዓመታት ተቆጠሩ፤ የሁለት አሥርተ ዓመታት የኢህአዴግ ጥረት ውጤቱ 10 ሚሊዮን ዜጋ በርሀብ አለንጋ ማስገረፍ ሆነ:: ተፈጥሮ ችራ የአዝዕርቱ ቅጠል ያማረ በመሰላቸው ጊዜ በምግብ ራሳችንን ቻልን እያሉ ሲባንኑ ቢባጁም፣ አልሆን ሲላቸው መረጃ አዛብተው ቁጥሩን ቢከምሩትም፣ በየሦስት ዓመቱ የሚሊዮኖችን መራብና በህዝብ ስም ጨርቅ ቀንሮ እርጥባን የመጠየቃቸውን ሀቅ ግን ሊደብቁት አልቻሉም::

ከሰሞኑ ደግሞ እያመማቸውም ቢሆን ሊደብቁት ያልቻሉት ሌላ የስርዓቱን ቀውስ ውስጥ መግባት የሚጠቁም ክስተት እየተስተዋለ ነው:: የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በፍጥነት እያደገ መሆኑንና በቅርቡም ሀገሪቱ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ እንደምትሰለፍ በታላቅ አጽንኦት በተናገሩበት፣ በተለይም ደግሞ የወጪ ንግዳችን እየተመነደገ እንደሆነ ባበሰሩበት አንደበታቸው አገሪቱ በከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ እጥረት ውስጥ መሆኗን እየገለጹ ነው:: ታማኝ ምንጮች እንደሚያመለክቱት የሀገሪቷ መጠባበቂያ የውጭ ምንዛሪ ተሟጧል:: የኢህአዴግ ባለሥልጣናት ለዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF) የተናዘዙትን በጥሬው ስንወስደው ሀገሪቱ ባሳለፈነው ታህሳስ ወር የነበራት የውጭ ምንዛሪ መጠባበቂያ ወደ 900 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚጠጋ ሲሆን፣ ይህ አብዛኛውን የገቢ ንግድ በመግታት ለይስሙላ የተቀመጠ ገንዘብ ከአንድ ወር የበለጠ የውጪ ግዥ ሊሸፍን አይችልም:: ሀገሪቱ ከሞላ ጎደል ወዴተረጋጋ ሁኔታ ለመመለስ ለሦስት ወር የሚበቃ የውጭ ምንዛሪ የሚያስፈልጋት ሲሆን የሥርዓቱ ሹመኞች በዚህ የበጀት ዓመት መጨረሻ ለአንድ ወር እንኳ የሚበቃ መጠባበቂያ ለመያዝ ነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ ላይ መሆናቸው ይነገራል::

ይህ እጥረት ቢያንስ ከስርዓቱ ተጠቃሚዎች ተርፎ ለተራው ህዝብ የሚንጠባጠበውን የውጭ ምንዛሪ በማሳጣት መዲሃኒትን የመሳሰሉ መሠረታዊ ፍጆታዎች ላይ ችግር ይፈጥራል:: የውጪ ምንዛሪ እጥረት ባለበት ሁኔታ የብር ቁልል ለህዝቡ እጅግ አስፈላጊ የሆነውን ነዳጅ ሊገዛ አይቻለውም:: በገቢ ንግድ ላይ የተመሠረቱ የግል የንግድ ተቋማትና የሚያስተዳድሯቸው ዜጎች በቀውሱ ምክንያት አደጋ ላይ ይወድቃሉ:: ለልማት ቅን የሆነ መንግሥት ባለበት አገር ሲሆን የሀገርን ልማት ይጎዳል:: ከሁሉም በላይ ግን ይህ ቀውስ ኢህአዴግ ቆርጦ ከሚቀጥለው በተቃራኒ በአገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ መፈጠሩን አመላካች ነው::

ከኢትዮጵያ አንጻር ዋና ዋናዎቹ የውጭ ምንዛሪ ምንጮች የወጪ ንግድ፣ የውጭ እርዳታና ብድር፣ እነዲሁም በውጪ አገር የሚኖሩ ዜጎች የሚልኩት ገንዘብ ናቸው:: ለእጥረቱ መፈጠር ከሚጠቀሱ ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ በአዝጋሚ የወጪ ንግድና ያለልክ በተንቦረቀቀ የገቢ ንግድ መካከል የተፈጠረ አለመመጣጠን ነው:: በተለይ የወጪ ንግድ ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) በመቶኛ ሲሰላ ላለፉት አምስት ዓመታት የነበረው ከቀዳሚዎቹ አምስት ዓመታት ጋር ሲነጻጸር በአንድ ከመቶ ብቻ የጨመረ ሲሆን ነገር ግን የገቢ ንግድ ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት በመቶኛ ሲሰላ በተመሳሳይ ወቅት በ9 ከመቶ ጨምሯል:: የውጭ ምንዛሪ ገቢ ከማስገኘት አንጻር የጀርባ አጥንት የነበረው የቡና ምርት በአሁኑ ጊዜ ከ60 ከመቶ በላይ እየቀነሰ እንደሆነና ከሱም የሚገኘው የውጪ ምንዛሪ ላለፉት ወራት በ44 ከመቶ እንደወረደ አንዳንድ ጥናቶች ያመለክታሉ:: በባለስልጣኖች ተጽዕኖ ምክንያት ብዙም እምነት የማይጣልበት የብሔራዊ ባንክ መረጃም የሚያሳየው በአለፉት ጥቂት ሩብ ዓመታተት ወደ ውጭ የተላከው ቡና የዛሬ ሁለት ዓመት በተመሳሳይ ወቅት ከተላከው በ18 ከመቶ የቀነሰ ሲሆን፣ በአለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅትም በቀዳሚው ዓመት ከነበረው መንፈቅ ዓመት በ25 ከመቶ ቀንሶ ነበር::

በተጨማሪም የበርካቶችን ሚና በጥቂት ባለሟሎች በተካውና በዘፈቀደ በተተገበረው የነኢሌኒ ገብረመድኅን የምርት ገበያ ውጥንቅጡ የወጣ አሠራር ምክንያት ቡና በህገወጥ መንገድ በገፍ ከሀገር መውጣት ለችግሩ አስተዋጽዖ እንዳለው ይነገራል:: በቅርቡ የሀገሪቱ የቡና ላኪዎች ከሥርዓቱ ቁንጮ ፊት ቀርበው እንደተናገሩት በአዲሱ አሠራር ከፍተኛ ችግር እየደረሰባቸው እንደሆነ ቢጠቁሙም ከአምባገነኑ መሪ አሳፋሪ ማስፈራሪያና ‹የእጅ መቆረጥ› ዛቻ ተሰንዝሮባቸዋል:: ይህ ዳር ዳርታም የቡና ዘርፉ የመለስ ቡድን በቀጣይ ሊገባበትና ሊቆጣጠረው ያሰበው ሌላ የዘረፋ መስክ ሊሆን እንደሚችል አመላካች ነው::

ለዚህ ቀውስ ማካካሻ ገቢ ያስገኛል ተብሎ ሲሞካሽ የነበረው የአበባ ልማትም ራሱ ለህልውናው የሚያሰጋ ሌላ ቀውስ ውስጥ በመግባቱ ችግሩን ሊታደግ አልቻለም:: በመስኩ የተሰማሩት ባለሀብቶች ትንሽ መነሻ ወረት በመያዝ አብዛኛውን የመዋዕለ ንዋይ ወጪ ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ በተገኘ ብድር በመሸፈናቸውና ብድራቸውን በወቅቱ ባለመመለሳቸው፤ እንዲሁም በተለይ የውጪ ባለሀብት ተብየዎቹ ትርፋቸውን በውጭ ምንዛሪ በማሸሻቸው የልማት መስኩ አጣብቂኝ ውስጥ ገብቷል:: በዚህ መስክ ተሰማርተው የነበሩ የውጪ አገር ዜጎችም አሻሮአቸውን ይዘው በመጠጋት ጤፍ ዘርፈው ሲሄዱ የኢህአዴግ ጉዶች መጀመሪያውኑም የፈለጓቸው ለርካሽ ፕሮፓጋንዳ ነበርና አይተው እንዳላዩ ሆነዋል::

በወጪ ንግድ ገቢ የገቢ ንግድን መሸፈን በሚያዳግትባት ኢትዮጵያ ልዩነቱን በመሸፈን ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱት ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማትና ለጋሾች እንዲሁም በውጭ የሚኖሩ ኢተዮጵያዊያን ናቸው:: እንዲህ እንደ አሁኑ የንግድ ሚዛኑ በከፋ ሁኔታ ሲዛባ ከነዚህ የውጭ ተቋማት ከሚገኘው የውጭ ምንዛሪ በተጨማሪ በውጭ አገር በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ይፋ ባልሆነ መንገድ የሚላከውን የውጭ ምንዛሪ በይፋዊ መንገድ ማዞር መቻል ከፍተኛ አስተዋጽዖ በኖረው ነበር:: ነገር ግን የውጪ ተቋማቱ አገዛዙ “የራስህን ህዝብ አታፍን፣ የምንሰጠውም እርዳታ ለህዝብ ጥቅም እንጂ ለገዢዎቹ ኪስ ማድለቢያ አይደለም“ በማለታቸው በትዕቢት አትድረሱብኝ ተብለዋል:: ከእርዳታ ዓይነትም ስብና ጉፋያ ሊያማርጥ የሚዳዳው ኢሕአዴግ ከዓለም ባንክና ከዓለም የገንዘብ ድርጅት እርጥባን ሲጠይቅ በሌላ በኩል ግን የልማትና ተራድዖ ድርጅቶችን ሚና የሚገድብ አፋኝ ሕግ ያወጣል:: ተቋማቱ ይህ ነውረኛ ሥርዓት አመጣሁ የሚለው ኢኮኖሚያዊ እድገት ፌዝና የአሀዝ ጨዋታ መሆኑን ዘግይተውም ቢሆን የተረዱት፣ ሥርዓቱን የሚሸከሙበት አንቀልባም የመነመነ ይመስላል:: ለምሳሌ የዓለም ባንክ ከአጠቃላይ የጥቅል ኢኮኖሚና የፋይናንስ አፈጻጸም፣ ከፋይናንስና ቴሌኮሚዩኒኬሽን ዘርፎች ሪፎርም፣ ከአፋኙ የሲቪክ ማኅበራት ሕግና ከአጠቃላይ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በተያያዘ ለሥርዓቱ ሊሰጥ የነበረውንና ኢህአዴግ ለዚህ ቀውስ መታደጊያ ይሆነው ዘንድ የቋመጠበትን በብዙ መቶ ሚሊዮኖች ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ አግዷል:: ብሂሉም ገላጭ ነው፤ “ገንዘብ የለሽ በራስ አታድሪ ጸባይ የለሽ ከሰው አትኖሪ“::

በሌላም በኩል በውጪ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንም እንደጠላት ተፈርጀው ሀገራቸው አስተዋጽዖ እንዳያደርጉ ተገድበው ኖረዋል:: ዛሬ ማጣፊያው ሲያጥረው እነዚህ ዜጎች ገንዘብ ወደአገር ቤት ሲልኩ ለእሱ ዕድሜ ማራዘሚያ ይሆነው ዘንድ በኦፊሴላዊ መንገድ እንዲጠቀሙ ፊቱን በጨው ታጥቦ መማጸን ጀምሯል::

ባህሪውን እንደእስስት በመቀያየር ወደር የማይገኝለት ይህ ሥርዓት ከቻይናና ከህንድ የምጽዋት እጅ የተዘረጋለት ሲመስለው ለነዚህ ተቋማት የገባውን ግደታዎች ለመቀልበስ ያለስንቅ እንዲዘምት ያደረገው የዱባ ጥጋብ ለጊዜው ባይበርድለትም፣ አንድ ነገር ግን የገባው ይመስላል፤ በአሃዝ ብቻ የተቆለለ የውጭ ምንዛሪ እንዳለ እያስመሰሉ መቀጠል እንደማይቻል:: የሌለ እድገት በአሃዝ አግዝፎ በማቅረብ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ማላገጥ ቢያንስ ለአሥራ ስምንት ዓመታት ሊያዋጣ ይችላል፤ አበዳሪ ተቋማትንም በዴሞክራሲ ስም እየማሉ፣ የእድገት አመልካች አሃዞቹንም እየፈበረኩ እነደዚሁ ለተወሰነ ጊዜ ማለዘብ ይቻል ይሆናል:: የሌለ የውጭ ምንዛሪ አለኝ ብሎ መኮፈስ ግን ግፋ ቢል ከሁለት ዓመታት በላይ አያዛልቅም:: ምክንያቱም ብቸኛው የውጭ ምንዛሪ አከፋፋይ ራሱ ስለሆነ እነደምርት እጥረቱ ‹ስግብግብ› በሚላቸው ነጋዴዎች ሊያመካኝ አይቻለውም::

ለነገሩ አገዛዙ እጥረቱን በፈረደበት ነጋዴ ለማሳበብ ሞክሮ ነበር:: ለበርካታ ዓመታት በአደባባይ የውጪ ገንዘብ ሲመነዝሩ አንድም ቀን በህግ ብሏቸው

የማያውቀውና ይልቁንም በስሙ ለሚያቋቁማቸው የዘረፋ ኩባንያዎች የሚውል የውጭ ምንዛሪ በስውርና በይፋ ከነዚሁ ነጋዴዎች ይገዛ የነበረው ይህ ስርዓት በነሸጠው ጊዜ ህገ ወጥ ናቸው ብሎ ማዋከብና ወደ እስር ቤት መወርወር አንድም እንደለመደው እጥረቱን በእነሱ ለማሳበብ፣ ሁለትም ለዘመናት ያጠራቀሙትን ጥሪታቸውን ለመቀማት ነው፡፡ ሕግና ኢህአዴግ አይተዋወቁም እንጂ ይህን እርምጃ የወሰደው ለሕግ የበላይነት መከበር ካለው ቀናዒነት ቢሆን ኖሮ በስውር ገበያው ቋንቋ "አስተማማኝ ናቸው" የሚባልላቸው የራሱ ምርጦችና ባለሟሎች በአደባባይ ይህንኑ ሥራ ሲሠሩ አይቶ እንዳላየ ባልሆነ ነበር፡፡ የኢህአዴግ የድረሱልኝ ጥሪ ሌላ የሚያመላክተው ቁም ነገር አለ፡፡ ለሕዝብና ለሀገር ተቆርቁሮ እንዳልሆነ ግን የራሱ ባህሪ ምስክር ነው፡፡ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ወገኖቻችን በረሀብ አለንጋ ሲገረፉ ሰብዓዊነትን ስለሚጠይቀው ችግራቸው ሳይሆን ስለቁጥራቸው አጀንዳ ፈጥሮ ከለጋሾች ጋር እሰጥ አገባ በመግባት በህይዎት ላይ የተዛበተ ሥርዓት፣ ከፉና ደጉን፤ ዘርና ፖለቲካን እንድሁም ጥላቻን ለይተው የማያውቁ ህጻናት በርሃብ ሲረግፉ ምናልባትም ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ቅንጦት ከሆነው የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ጋር በማያያዝ ያላገጠ አገዛዝ የአሁኑን ቀውስ አምኖ አስቸኳይ እርዳታ መጠየቁ ከቅንነት የመነጨ ሊሆን አይችልም፡፡ ስርዓቱን ያስጮኸው ይህ እጥረት የራሱን ለከት ያጣ ጥቅም የሚነካ የመሆኑ ዕውነታም ጭምር ነው፡፡

ኢህአዴግ በራሱና በባለሟሎቹ አማካይነት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ የበላይነቱን ለማረጋገጥ በአስገራሚ ፍጥነት የሚራወጥበት ወቅት ነው፡፡ ለእጥረቱ መፈጠር አንዱም ምክንያት ይሄው ስግብግብነት ሲሆን እጥረቱ ደግሞ ህልሙን ለማረጋገጥ የሚያደርገውን ሩጫ ይገታበታል፡፡ ለዚህም ‹የተጀመረው ፈጣን እድገት ሊቆም ነው› በሚል የብልጥ ጩኸት የዓለም አቀፍ አበዳሪዎችን ዳግም ማጭበርበር ግድ ይለዋል፡፡

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ይህ የውጭ ምንዛሪ እጥረት የተከሰተው ቢያንስ ከሁለት ዓመት በፊት ጀምሮ ነው፡፡ በውሸት የተካበው የኢኮኖሚ እድገት ተረት ተረት እንዳይጋለጥ በሚል ግብዝነት የአንድን ሀገር ደህንነት በእጅጉ የሚፈትን የዚህን ዓይነት ቀውስ እስኪከሰት ድረስ መጠበቅ የስርዓቱን ግድየለሽነትና ለሀገር ያለውን ደንታቢስነት ያሳያል፡፡

## በትግራይ የዲሞክራሲ...(ከገጽ 1 የዞረ)

(ከገጽ 1 የዞረ)

ተሰብሳቢዎች አቶ ገብሩ አስራትን የተለያዩ ጥያቄዎችን የጠየቋቸው ሲሆን በተለይ ወያኔ በባደመ ጥይቄ ዙሪያ ነደፎ ያስቀመጠዉን አምስት የ"ሰላም" ሃሳቦች በመቃወም በአዲስ አበበ መስቀል አደባባይ በተዘጋጀዉ ሰላምዊ ሰልፍ ላይ «ጠላት ከሆኑት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ተገኝተዉ ለምን ንግግር አሰሙ?» ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ሲመልሱ "ኢትዮጵያዉያንን እስከሆንን ድርስ ትግራይ መሬታችን ነዉ። ኦሮሚያ መሬታችን ነዉ። ደቡብ ና ሶማሊያ መሬታችን ነዉ። አፋርም መሬታችን ነዉ። ለነርሱም ትግራይ መሬታቸዉ ነዉ። አማራም ትግራይ መሬቱ ነዉ። ሊኖርበት ይችላል። በዚህ ማመን አለብን። ከዚህ ዉጭ የፖለቲካ ተቃዋሚ ድርጅቶችን እንደጠላት ለማስፈራሪያ መጠቀም የሥልጣን እድሜን ማራዘሚያ እሆኑ መታወቅ አለበት። አሁንም በሰላምዊ ትግል ካመኑትና ሕጋዊ ፈቃድ ካገኚኡት ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር አብረን መሥራት እንቀጥላለን።"በማለት መመለሳቸው ተያይዞ ተገልጿል።

ይህ በወያኔ ጎራ ትልቅ ሽብር ብቻ የሚነዛ ሳይሆን ከ ቀራቸውና ህዝቡን በተሳሳተ መረጃ በማደናገር ከሚኩራሩበት ብቸኛው የድጋፋቸው ምንጭ ሀቁን በማጋለጥ ነቅሎ የሚጥላቸው እንቅስቃሴ መሆኑን የሚናገሩ አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች በተለይ የትግራይ ወንድሞቻችን ሀቁን እየተረዱና ለሚደረገው የነጻነት ትግል ከቀሪው ወንድሞቻቸው ጋር ለመታገል ሲነሳሱ ማየት እጅግ አስደሳች መሆኑን ሲገልጹ ተደምጠዋል።

አረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ልሉአላዊነት ፓርቲ በስብሰባው የብዙዎችን ቀልብ እንደገዛና ከፍተኛ ድጋፍ እንዳገኘም አንዳንድ ከአካባቢው የሚወጡ መረጃዎች ጠቁመዋል።

## ወያኔ፤ሼህ ... (ከገጽ 2 የዞረ)

ውያኔ ህዝቡን በዘር ለመከፋፈል ይመቹኛል የሚላቸውን አሻንጉሊቶች በየመስሪያቤቱ ሰግስጎ የመከፋፈል ሙከራ ሲያደርግ መቆየቱ አልበቃ ብሎት ይህ አልሰራ እንዳል ሲረዳው ደግሞ ያለ የሌለውን አቅሙን በመጠቀምና በየሀይማኖት ድርጅቶች ከፋፋይ አሻንጉሊቶችን አመራር ቦታ ላይ በማስቀመጥ ህዝቡን በሀይማኖት ለማጋጨት ሙከራ እያደረገ መሆኑ ይታወቃል።

በተለያየ ጊዜ የእምነቱ ተከታዮች ሼክ ኤሊያስ ሬድዋንን የወያኔ ካድሬ በመሆናቸውና የሀይማኖቱን ጥቅም ከማስጠበቅ ይልቅ ወያኔ የሚያስተላልፈውን የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ በማራመዳቸው ከፍተኛ ጥላቻና ተቃውሞ እንዳላቸው በመግለጽ አሁን የተደረገውን ሹም ሽር እጅግ እንዳስደሰታቸው ጠቁመዋል። ሼክ ኤልያስና ውርደት የማይሰለቻቸው የወያኔ ባለስልጣናት ምን አይነት እርምጃ ይወስዳሉ ተብሎ በሁሉም እየተጠባበቀ መሁኑንም አያይዘው ገልጸዋል።

## ከአድማጫችን የተላከልን ግጥም

### አለቅም

የባርነት ገዳም መነኩሴው፣
የሞት ፀበል የሚያጠምቀው፣
የክህደት ዘንጉን ጨብጦ፣
የደም ቆቡን ደፍቶ፣
በቡትቶ መጎናፀፊያው.....ተደርቶ።
ታማሚውን....... ዋርካውን ፣
የነፃነት ዛር ማረፊያውን
ከተጠናወተው አባዜ........ከነጻነት ደዌ ሊያላቅቀው፣
ውጣ ይለዋል የባርነት ገዳሙ መነኩሴ.......የባርነት ፀበሉን እየረጨው።
የነፃነቱ መንፈሱ እያጓራ፣
እየተወራጨ ቀኝ ግራ ፣
የአያት ቅድም አያቱን ስም እየጠራ፣
የቤት ጣጣ ነኝ ብያለሁ
ሀረግ ስቤ የመጣሁ፣
እሱን አሳድጌ፣
ሲሻኝ ዋርካዬ ........ሲሻኝ ፈረሴ አደርጌ።
ከትውልድ ትውልድ.... ተሻግሬ የተሻገርሁ፣
ስነግስ ስከብር........... ኖሬ የኖርሁ።
በባህር በምድር ባየር ....... ስጋልበው እያየህኝ።
ወዲያ በል አለቅም .......የቅድመ አያቶቹ መንፈስ ነኝ፣

ከአብርህም ዘገየ

ጥቅምት 5 2001 አዲስ አበባ

የነፃነት ዛር ለተለከፉ ስለምንም ነገር ነፃነቴን አሳልፌ አልሰጥም ብለው ለሚታገሉ ኢትዮጵያውያን በሙሉ መታሰቢያ


የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ
የሥርጭት ሞገድ ለውጥ አድርጓል።

በዚሁ መሰረት ከአሁን ቦኋላ በ7485 KHZ በ41 ሜትር ባንድ እና በ9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።